# አዲስ አሠራር፣-አዲስ ፈጠራ፣ የትምህርት ዓመት ካለንደር ያላቸው ትምህርት ቤቶች የተለያዩ መረጃዎች ዝርዝር እና ስለ ተማሪ ብህትውነት-Privacy አመታዊ መግለጫ

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Rockville, Maryland 20850
የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፕእብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንብ JOA-RA፣ የተማሪ መረጃ/ሪከርድ

**የቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶች እና ብሕትዉነት ህግ/ Privacy Act (FERPA)፣ (20 U.S.C.§1232g፣ 34 CFR ክፍል 99) ያለዎትን መብቶች ስለማሳወቅ የተዘጋጀ አመታዊ መመርያ ለማየት ግልባጩን ገጽ ይመልከቱ**

**ማዉጫ**

ትምህርት ቤቶች የማንነት መረጃዎችን ይፋ መዛግብት/ሪከርድ፣ ለኦነር ሮል ሽልማቶች፣ እና ሌሎችም በጋዜጣ ወይም የሞንትጎሞሪ ፐእብሊክ ስኩልስ (MCPS) ድረ ገጽ ማስታወቂያዎች ለመሳሰሉት ዝርዝር መረጃዎችን ይሰጣሉ። የተማሪ ስም፣ አድራሻ፣ እና የስልክ ቁጥር መረጃ ለማንኛውም ለወላጆች/አሳዳጊዎች፣ አስተማሪዎች፣ እና የትምህርት ቤት ተማሪዎች አካል ድርጅቶች ይፋ ሊደረግ ይችላል። በእርስዎ በኩል ተቃውሞ ከሌለ በስተቀር፣ ት/ቤቶች መረጃውን ያለርስዎ ፈቃድ ሊያስተላልፉት/ሊገልፁ ይችላሉ።

የመረጃዎች ዝርዝር የሚከተሉትን ያካትታል፡- የተማሪ እና/ወይም የወላጅ/አሳዳጊ ስም፣ አድራሻ፣ የኢሜል አድራሻ እና ስልክ ቁጥር፤ የተማሪን የልደት ቀን፤ የጥናት መስክ፣ የክፍል ደረጃ፣ በሚታወቁ እንቅስቃሴዎች እና ስፖርቶች ውስጥ የተሳትፎ ሁኔታ፣ ዲግሪዎች እና ሽልማቶች (ኦነር ሮል ጨምሮ)፣ በቅርብ ጊዜ የተማሪ(ች)በት ትምህርት ቤት፣ የተማሪ(ች)በት ጊዜ፣ ፎቶግራፍ፣ ወይም ሌላ ተመሣሣይ መረጃ፣ የአትሌቲክስ ቡድን አባላት ክብደት እና ቁመት፣ እና ሌሎች ተመሳሳይ መረጃዎች።

ትምህርት ቤትዎ የተለያዩ መረጃዎችን ዝርዝር ይፋ እንዳያደርግ ከፈለጉ፣ ከዚህ በታች ያለውን ቅጽ ሞልተው ከጁላይ 19/2024 በፊት ለትምህርት ቤትዎ ይመልሱ።

የዚህ ማስታወቂያ ተጨማሪ ቅጆዎች MCPS ድረ-ገጽ ላይ ይገኛሉ፣ እናም በእስፓንሽኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በቬትናሚስ፣ በቻይንኛ፣ በኮሪያኛ እና በአማርኛ ቋንቋዎች ይገኛሉ።

ይህ ቅጽ በየአመቱ መሞላት አለበት።

ለእርስዎ ትምህርት ቤት ይህ ቅጽ እስከ ዓርብ፣ ጁላይ 19/2024 ተሞልቶ ካልተመለሰ የተለያዩ መረጃዎች ዝርዝር ይፋ እንዲደረግ እንደተስማሙ ተደርጎ ይቆጠራል

በሌላ ጊዜ ሀሳብዎን መቀየር ከፈለጉ ትምህርት ቤትዎን በቀጥታ ያነጋግሩ።

የሚያስመዘግቡት ከጁላይ 19/2024 በኋላ ከሆነ፣ ይህንን ቅጽ በምዝገባ ወቅት ለመሙላት ይችላሉ።

Montgomery County Public Schools
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
2024-2025 የትምህርት አመት ግላዊ መረጃ እንዳይሰጥ ስለመጠየቅ

ከሚከተሉት አንዱን ይምረጡ፡-

❑ እባክዎ ማንኛውንም ግላዊ መረጃ እንዳይሰጡ። (ዝርዝሩን እላይ ይመልከቱ)

❑ እባክዎ የሚከተለውን ግላዊ የመረጃ ክፍል ወይም የመረጃ ክፍሎች አይስጡ። (በሚመለከተዉ ሁሉ ላይ ምልክት ያድርጉ)
❑ ስም ❑ ስልክ ቁጥር(ሮች) ❑ ፎተግራፍ ❑ አድራሻ ❑ የተዉለድ ቀን
❑ የኢሜይል አድራሻ ❑ የወላጅ/አሳዳጊ ስሞች ❑ የክፍል ደረጃ

እንዳይሰጥ ከተጠየቀዉና እላይ ከተጠቀሰው በስተቀር፡-

❑ ለማናቸውም የትምህርት ቤት ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ መምህራን፣ እና ተማሪዎችን ለሚመለከቱ ድርጅቶች ይፋ ይደረግ

❑ ለኦነር ሮል መጽሔት ይፋ ይደረግ ❑ ለአመታዊ-መጽሔት ፎቶ ይሰጥ

የተማሪ ስም ______________________ የክፍል ደረጃ______ መታወቂያ ቁጥር________)________

ትምህርት ቤት ______________________________________

የወላጅ/አሳዳጊ/ብቁ ተማሪ ፊርማ ______________________ ቀን____/____/_____

ስለ ልጅዎ የተወሰኑ መረጃዎች እንዳይሰጡ ካልገደቡ በስተቀር፣ እያንዳንዱ ግላዊ መረጃ የወላጅ ፈቃድ ሳይጠይቅ የእለት ስራ ክንውኖችን እና መደበኛ ስራቸውን እንዲሠሩ ለትምህርት ስርአቱ እና የአካባቢ ትምህርት ቤቶች አዎንታ እየሰጡ ነው።

# FERPA * መብትዎን የሚገልጽ አመታዊ ማስታወቂያ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ እንደመሆንዎ መጠን የልጅዎን የትምህርት ሪኮርዶች በተመለከተ Family Educational Rights and Privacy Act (በቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶች እና ግላዊነት ህግ) (FERPA)፣ አግባብነት ባላቸው የፌደራል ደንቦች እና Code of Maryland Regulations (በመመሪያ አውጭው አካል ስም የተደራጀ የሜሪላንድ ህግ መመሪያዎች) (COMAR) 13A.08.02 መሠረት የተወሰኑ መብቶች አለዎት። እነኝህ መብቶች ከዚህ በታች በአጭሩ የተገለጹ ሲሆን እንዲሁም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መመሪያ JOA-RA፣ ስለ ተማሪ ሪከርድ www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/joara.pdf በዝርዝር ተገልጿል።

1. የተማሪ ሪከርዶች ግምገማ። የልጅዎን የትምህርት ሪከርዶች ትምህርት ቤቱ የእርስዎን የጽሁፍ ጥያቄ ካገኘ ከ 45 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የመፈተሽ እና የመገምገም መብት አለዎት። ትምህርት ቤቶች በተቻለ መጠን የጽሁፍ ጥያቄ በደረሳቸው 10 ቀናት ውስጥ፤ የተማሪን መለያ፣ ግምገማ፣ ወይም ከምደባ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ስብሰባ ከመደረጉ አስቀድሞ እንዲከናወኑ ማድረግ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ግብ ነው። ትምህርት ቤቱ የልጅዎን መረጃዎች የሚያገኙበትን እና መዝገቦችን የሚያዩበትን ጊዜ እና ቦታ በማመቻቸት ያሳውቅዎታል። በዚህ ግምገማ ወቅት ርእሰ መምህሩ/ሯ ወይም ተወካይ ይኖራሉ።

2. የተማሪ ሪከርዶች ማሻሻያ። የልጅዎ ሪከርዶች ትክክል ካልሆኑ፣ የተሳሳቱ፣ ወይም የልጅዎን ግላዊ መብቶች እንደሚጻረሩ ካመኑ፣ ትምህርት ቤቱ ሪከርዶቹን እንዲያሻሽል የጽሁፍ ጥያቄ የማቅረብ መብት አለዎት። የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንብ JOA-RA፣ የተማሪ መዛግብት/ሪከርዶች፣ እንደ አግባብነቱ ቅሬታ ማቅረብን ጨምሮ፣ ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ የመስጠት አሰራሮችን ይዘረዝራል። በዚህ ደንብ መሰረት ውጤቶች ለድርድር አይቀርቡም።

3. የተማሪን ሪከርዶች/መዛግብት ይፋ ማድረግ። በፌደራል ወይም የስቴት ህግ ያለፈቃድ እንዲገለጽ ወይም በተለይ የተፈቀደ ካልሆነ፣ በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የግለሰብ መረጃ ከልጅዎ የትምህርት ሪከርዶች/መዛግብት ይፋ ከመደረጉ በፊት የፅሁፍ ፈቃድ የመስጠት መብት አለዎት። ስለ መረጃ አሰጣጥ መመሪያዎች፣ እንዲሁም መረጃ እንዳይገለጽ ያለመስማማት ሁኔታን የሚገልጽ በዚህ ቅጽ በስተጀርባ ተጠቅሰዋል። በተጨማሪ፥ ለመገንዘብ የሚያስፈልግዎት ነገር፤ ህጋዊ የትምህርት ሃላፊነት ላላቸው፣ ** የትምህርት ቤት የስራ ሃላፊዎች፣ አስተዳዳሪዎች፣ መምህራን፣ ወይም በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለተቀጠሩ ሰራተኞች (መረጃ) ለመስጠት ስምምነት እንደማያስፈልግ ያስተውሉ። ይኼውም የሚከተሉትን ሌሎች ስለ MCPS የሚሰሩ የስራ ሃላፊነታቸውን ለመወጣት መረጃ ማግኘት የሚያስፈልጋቸውን ይጨምራል፡ በትምህርት ቤት የጤና አገልግሎት ሠራተኞች፣ እና የጤና ባለሙያዎች፣ የት/ቤት የጥበቃ ሠራተኞች፣ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ አባል፣ግለሰብ፣ ድርጅት፣ ወይም በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እንዲሰሩ ኮንትራት የተቀጠሩ ካልሆነም የሞንትጎሞሪ የሕዝብ ት/ቤቶች የራሱን ቅጥር ሠራተኞች (ዓቃቤ ሕግ፣ ወይም ኦዲተሮች)፣ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ሌላ በፈቃደኝነት ሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ በኮሚቴ የሚያገለግል ወይም ሌሎች በትምህርት ዘርፍ በመርዳት የሚያገለግሉ።

   ጥያቄ ከቀረበ፣ የትምህርት መረጃዎችን፣ ለሌሎች ት/ቤቶች፣ ለትምህርት ዲስትሪክት፣ ወይም ከሁለተኛ ከረጃ በላይ ላሉ የትምህርት ተቋማት፣ የተማሪ መረጃ የተፈለገው ለትምህርት ምዝገባ ወይም ወደ ሌላ ት/ቤት፣ የትምህርት ዲስትሪክት፣ ወይም ሌላ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ለመዛወር ከሆነ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ያለ ፈቃድ መረጃ መስጠት ይችላል። በተጨማሪ፣የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በህጋዊ መንገድ ከተማሪ ሪከርዶች/መዛግብት ላይ ስለ ግለሰብ የሚገልጹ መረጃዎችን፣ ከእርስዎ በቅድሚያ የጽሁፍ ስምምነት ሳይኖር ልዩ መንግስታዊ ኤጀንሲዎች፣ የተፈቀደላቸው የምርምር ፕሮጀክቶች፣ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ወይም ህጋዊ የፍርድ ቤት መጥሪያ፣ ወይም የጤና ወይም ድንገተኛ የደህንነት አደጋን ጨምሮ FERPA ለፈቀደላቸው ሌሎች ምክንያቶችም ሊገልጽ ይችላል።

   ተጨማሪ መረጃ MCPS ደንብ JOA-RA፣ የተማሪ ሪከርዶች/መረጃዎች MCPS ድረ-ገጽ ላይ ወይም በእርስዎ የአካባቢ ትምህርት ቤት ይገኛል።

4. ለዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት የሚቀርብ አቤቱታ FERPA ያሉዎት መብቶች እንደተጣሱ ካመኑ እና ጉዳዩ በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የይግባኝ ደረጃዎች ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶች አጥጋቢ ካልሆኑ፣ በዩ.ኤስ. የትምህርት ዲፓርትመንት የቤተሰብ ፖሊሲ አፈጻጸም ጽ/ቤት Family Policy Compliance Office in the U.S. Department of Education, 400 Maryland Avenue, SW, Washington, DC 20202-5920 ወይም 1-800-USA-LEARN (1-800-872-5327) በመደወል አቤቱታ የማቅረብ መብት አለዎት።

* ብቁ ተማሪዎች ያሏቸው መብቶች፡- እላይ የተገለጹት መብቶች 18 አመት ለሆነ/ች ወይም ድህረ ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ተቋም በመማር ላይ ለሚገኝ/ለምትገኝ ተማሪ ይሰራል። ነገር ግን ብቃት ቢኖራቸውም በወላጆቻቸው ጥገኛ የሆኑ ተማሪዎች ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው ብቁ ከሆነ(ች) ተማሪ የቅድሚያ ስምምነት ሳያስፈልጋቸው የልጃቸውን መረጃ/መዛግብት ለማየት ይችላሉ።

** የትምህርት ቤት ባለስልጣናት ሙያዊ ኃላፊነትን ለማከናወን የትምህርት መረጃዎችን/መዛግብት ማየት እና መገምገም ካስፈለጋቸው መረጃዎችን የማግኘት አጠቃላይ ህጋዊ የትምህርት ሙያ ሃላፊነት አላቸው።